# ሰሞነኛ

## «በሰላምና በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የዲያስፖራው ተርታ»

**በሎስአንጀለስ የኢትዮጵያ**

**ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት**



**Consulate General of Ethiopia**

**3460 Wilshire Blvd #308**

**Los Angeles, CA 90010**

**Tel: (213) 365 - 6651 Fax: (213) 365 - 6670**

www.ethioconsulate-la.org

**ሚያዚያ /2002**

**April/2009**

# «በሰላምና በዴሞክራሲያዊ ምርጫ የዲያስፖራው ተርታ»

የኢትዮጵያ መንግስት የአገራችን የልማት፣ዴሞክራሲና የሰላም ግንባታ በእጅጉ የተያያዙና የተቆራኙ መሆናቸውን ሳይታክት ሲያስገነዝብና ለዚሁም በትጋት ሲሰራ መቆየቱ የሚታወቅ ነው።በአገራችን ፈጣን ልማትን ለማምጣት አስተማማኝ ሰላምና ዴሞክራሲን መገንባት መሰረት የሆነውን ያህል፣ የተረጋጋ ሰላምና የተባ ዲሞክራሲን ለማስፈን ደግሞ አሰተማማኝ ልማትን ለማረጋገጥ ማገርና ቋሚ መሆናቸውን የሚስተው የለም። ለዚህም ነው የአገራችን የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም ግንባታ እንቅስቃሴዎች አንድም ሦስትም ናቸው የሚባለው። ባለፉት 18 ዓመታት ለልማትና ለዕድገት የተደረገውን ውጣ ውረድ ያህል ለሰላምና ለዴሞክራሲያዊ ግንባታም እንዲሁ ተደርጓል። አገራችን ለተከታተይ 7 ዓመታት ያስመዘገበችውና በማስመዝገብ ላይ ያለችው የባለ ሁለት አሀዝ ዕድገት፣ በአስተማማኝ ሰላም የተገኘ ውጤት ነው። የልማት ዕድገታችን ሳናቋርጥ ባከናወናቸው የሕዝብ ተሳትፎዎችና ህገ መንግስቱ ባስቀመጣቸው ዴሞከራሲያዊና የሰብዓዊ መብት ክንውኖች ተመጋጋቢነት የተገኘ ውጤት ነው። አሁን የሚካሄደው የምርጫ ሂደትም የዚሁ ባለ ዘረፈ ብዙ እንቀስቃሴ አካልና የዲሞክራሲ ግንባታ ጉዞአችን መግለጫ ነው።

ህገ-መንግስታዊ ሥርዓት መከተል ከጀመርን ወዲህ  የዘንድሮውን ምርጫ ሳይጨመር ሦስት ብሄራዊና አገራዊ ምርጫዎች ተካሂደዋል። እንደሚታወቀው በአገራችን ድህነትን ታግሎ ወደ ልማት መጓዝ ዋና ተግባር የሆነውን ያህል፣ ዴሞክራሲዊ ስርዓትን የመትከል ጉዳይም ብዙ ሳንካዎችን እየተሻገረ እንዲጓዝ የግድ የሚል ክንውን ሆኗል።በምርጫዎች የሚሳተፉ የፖለቲካ ድርጅቶች ከግዜ ወደ ግዜ በቁጥር ማደጋቸው የሚታይ ቢሆንም፣ያዳበሩት ዴሞክራሲዊ የትግል አግባብ ግን እንደየፓርቲዎቹ ርዕዮት፣ የትግል አግባብና የመሪዎቻቸው ጥንቅር ሳቢያ በአመዛኙ በችግር የተተበተበ ነው።ያም ሆኖ በሰላማዊ የዴሞክራሲዊ ውድድር ብቻ የሚያምኑ ልማትና ዲሞክሲያዊ ምርጫ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን የሚረዱ ድርጅቶች ከጉድለታቸው እየተማሩ በመድበለ ፓርቲ አግባብ ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲ እንዲያብብ ለማድረግ የማይተካ ሚና ይኖራቸዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ህገ መንግስቱን ተቀብለው በማደር ነፃና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የፖለቲካ ስልጣንን ሊይዙ ፈቅደው ከተመዘገቡና ህጋዊ ዕውቅና አግኝተው ወደ ውድድር ከቀረቡ በኃላ ሁለት መንገድ ያለው የትግል አግባብ ሊይዙ ከቶ አይገባም።«ሁለት ሞርድ አንዱ ቢደንዝ በአንዱ ጉረድ» አይነት ታክቲክ አንድም ኃላቀርነት ያለያም ቱባ ነውጠኝነት ይሆናል። በሰላምና በዴሞክራሲዊ አግባብ የሚደረግ ህዝባዊ ትግል ብቻ ነው ውጤታማና ተቀባይነትን ሊያስገኝ የሚቻለው።

ካለፉት ምርጫዎቻችን የታዩ ጉድለቶቻችን በማረም ተቃዋሚ ድርጅቶችም ሆኑ ገዢው ፓርቲ በጋራ በመምከር የምርጫ ስነምግባር ህግ በማውጣትና የምርጫ ም/ቤት በማቋቋም የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት የሚያደርጉት ጥረት ሊጎለብት የሚገባ ነው። ይህ በጎ ተመክሮ ከምርጫው በኃላም ጠንክሮ በመቀጠል ለልማትና ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

በሌላም በኩል ከውጭ ሀይላት ጋር አስፈላጊ በሆነበት መልክና ዴሞክራሲዊ አካሄዳችን እስከአጎለበቱ ድረስ በጋራ መስራቱና መደጋገፉ የሚበረታታ ቢሆንም፣ የአገራችን መፃዒ ጉዞ በመወሰን ረገድ ግን በፈለጉት መልክ የሚያሾሩን መሆን እንደማንችል የኢትዮጵያ መንግስት በሚከተለው መርሆም ሆነ በተግባር በወሰዳቸው አቋሞች አረጋግጧል። መንግስት የብሄራዊ ማንነታችንና ክብራችንን የሚፈታተኑ ጉዳዮችን የማይቀበል መሆኑ አያሌ አብነቶችን ነቅሶ ለማሳየት ይቻላል። ስለዚህ ጥቂት ቀናት የቀሩትን አገራዊ ምርጫ በመንተራስ ባዕድ የሆኑ ጥቅሞች ለማራመድ ወይም የራስን የአስተሳሰብ ርዕዮት መነሻ በማድረግ የሚመጡ የውጭ ወከባዎችን፣ ተፅዕኖዎችን በመመከት ደረጃ በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ጉልህ ሚና እንደሚኖረው የሚያጠያይቅ አይሆንም።

በውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውን የአገራችን ልማት እንደሚመለከተን ሁሉ የተረጋጋ ሰላሟና የዳበረ ዴሞክራሲዊ ግንባታዋም ይመለከተናል። የዳበረ ዴሞክራሲያዊ ባህል ይታይባቸዋል ተብለው በሚጠቀሱ አገሮች የምንኖር ወገኖች እንደመሆናችን መጠን የአገራችን ምርጫ ሰላማዊ፣ዴሞክራሲያዊና የሰከነ ሆኖ እንዲከናወን ማበርከት የሚገባንን ሚና ለይተን አስተዋፅኦ ልናደረግ ይገባል።እያወቁም ሆነ ሳያውቁ የምርጫ ወቅትን በመጠቀም የአገራችን ገፅታ ለማበላሸትና በዓለም አገራት ፊት መዘባበቻ ለማድረግ የሚደረገውን ሴራ ልናከሽፍ ይገባል።«እኛ ከሌለንበት» አይነት ያጥፊነት አባዜ የሚያንገላታቸውን ወገኖቻችን በዝምታ የምናልፍበት ጊዜ ማክተሙን የጀመራናቸውን እንቅስቃሴዎች በማጠናከር

ማስመስከር ይኖርብናል ። ምርጫን በማስታከክ ህግ እንዲጣስ ሰላም እንዲታወክ ልማታችን እንዲያናጥብ በአደባባይ የሚሰብኩትን አሳምረን እናውቃቸዋለንና ቢያንስ አደብ ይገዙ ዘንድ ልንነግራቸው ይገባል።